# ምን ብሉ ነበር?

ለዚህ ለአሁኑ እትም የወሰድናቸው ጥቅሶች በጠቅላላው በ1963 በወቅቱ ለቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርስቲ ቻንስለር ስለከፍተኛ ትምህርት የተቋቋመው አማካሪ ኮሚቴ ካቀረበው ሁለተኛ ራፖር ነው ።

" በጠቅላላው በኢትዮጵያ ትምህርታዊ ፕሮግራም ውስጥ የመምህራን መሠልጠን ከሁሉም ይልቅ ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው ብለን እንገምታለን ። በደንብ የሚዘጋጁ መምህራን የሚበቃውን ያህል ካልተገኙ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስንኩል ይሆናል፤ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡትም ተማሪዎች ለዚህ ሥራ በዝግጅት በኩል ብስል ተቀሊል ይሆናሉ ።" ገጽ 9.

*   *   *

" ምርምር ማድረግ የአንድ በከፍተኛ ደረጃ የሚገኝ ዩኒቨርስቲ ዐቢይ ሙያ መሆኑን እንገነዘባለን። ...በልዩ ልዩ መንገድ ሊደገፍ የሚቻልና የሚገባው ነው ። ይህም

- አሁን የሚሠራበትን የዐረፍትና የምርምር ፈቃድ ፕሮግራም እንዲቀጥልና እንዲስፋፋ በማድረግ
- ለጽሑፍ ማሳተሚያ አንድ ዓይነት ጥሬ ገንዘብ በማደራጀት
- መምህራኑ የሚያካሂዱትን የምርምር ሥራ ለማገዝ ከዩኒቨርስቲው ውጭ ገንዘብ በመፈለግ፣
- መምህራኑ በገንዘብ በደንብ በተደገፉና በመካሄድ ላይ በሚገኙ ሥራዎች ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ እንዲሰሩ በማድረግ፣
- ለምርምርና ለጥናት እቅዶች ማኅበሪያ የሚያገለግል የመነሻ ጥሬ ገንዘብ ዝግጁ በማድረግ" ። ገጽ 14.

*   *   *

# <u>ምን ብለው ነበር</u>?

> ለዚህ ለአሁኑ እትም የወሰድናቸው ጥቅሶች በጠቅላላው በ1963 በወቅቱ ለቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርስቲ ቻንስለር ስለከፍተኛ ትምህርት የተቋቋመው አማካሪ ኮሚቴ ካቀረበው ሁለተኛ ሪፖርት ነው ።

" በጠቅላላው በኢትዮጵያ ትምህርታዊ ፕሮግራም ውስጥ የመምህራን መሠልጠን ከሁሉም ይልቅ ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው ብለን እንገምታለን ። በደንብ የሚዘጋጁ መምህራን የሚበቃውን ያህል ካልተገኙ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስንኩል ይሆናል፤ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡትም ተማሪዎች ለዚህ ሥራ በዝግጅት በኩል ብስል ተቀሊል ይሆናሉ ።" ገጽ 9.

* * *

" ምርምር ማድረግ የአንድ በከፍተኛ ደረጃ የሚገኝ ዩኒቨርስቲ ዐቢይ ሙያ መሆኑን እንገነዘባለን። ...በልዩ ልዩ መንገድ ሊደገፍ የሚቻልና የሚገባው ነው ። ይህም

- አሁን የሚሠራበትን የዕረፍትና የምርምር ረቂቅ ፕሮግራም እንዲቀጥልና እንዲስፋፋ በማድረግ
- ለጽሑፍ ማሳተሚያ አንድ ዓይነት ጥሬ ገንዘብ በማደራጀት
- መምህራኑ የሚያካሂዱትን የምርምር ሥራ ለማገዝ ከዩኒቨርስቲው ውጭ ገንዘብ በመፈለግ፤
- መምህራኑ በገንዘብ በደንብ በተደገፉና በመካሄድ ላይ በሚገኙ ሥራዎች ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ እንዲሰሩ በማድረግ፤
- ለምርምርና ለጥናት እቅዶች ማኣበሪያ የሚያገለግል የመነሻ ጥሬ ገንዘብ ዝግጅ በማድረግ" ። ገጽ 14.

* * *

" በተለይ በየዓመቱ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥር እየበረከተ የሚሄድ ከሆነ በዩኒቨርሲቲው የሚገቡት ተማሪዎች ከተፈላጊው ደረጃ የደረሱ ለመሆናቸው አስፈላጊው አስተያየት እንዲሰጠው ያስፈልጋል። ... የአሁኑ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ጥራት ተለይቶ እንዲታወቅ ደረጃው በተወሰነለት ፈተና ጥናት እንዲደረግ ሃሳባችንን እናቀርባለን።" ገጽ 22.

* * *

" ዩኒቨርሲቲው ወደፊት ለሚያደርገው ለማት ሊደገፍ ከሚገባው ለውጥ መካከል አንዱና ዋናው በዛ ያለውን አጽንዖት በመምህራኑ ማስተማር ላይ ከማድረግ ይልቅ <u>በተማሪዎች ማጥናት</u> ላይ ማድረጉ ነው። ይህም ሊከናወን የሚቻለው፤

- በክፍል የሚሰጠውን ትምህርት ረገጥን ከነቢብ ወደ ልዩ ልዩ ስልቶች መለወጥ፤ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል። የተመራ የመስክ ሥራና የተቀየደ ንባብ፣ በጓድ በጓድ የሚሠሩ ሥራዎች፤ የጉዳይ ጥናት፤ በቡድን በቡድን ማስተማር፤ በትምህርታዊ ቴክኒኮች በመጠቀም ጉባኤ፣ ጥናቶችና ሌሎችም የመደበኛው "ማስተማር" ተለዋጮች ናቸው።

- ነፃ የሆነ ገለ–ሰባዊ ጥናት

- ተማሪ ተማሪን፣ /አንጋፋው ደቂቁን/ እንዲያስተምር በማድረግ፣ ማስተማር የማጥናት መዘከር ይሆናል

- እየሠሩ የማጥናት ፕሮግራሞችን ማበረታታት

- የትምህርት ፋኩልቲ ባቀረበው ሐሳብ መሠረት የሳይንስ ማስተማሪያና የሥርዓተ ትምህርት ድርጅት መመሥረት

- ተማሪዎች በመማር በኩል የባለጠ ኃላፊነት እንዲሰማቸው የሚያገዙ ዘዴዎች በማደራጀት ነው።" ገጽ 14 ና 15

* * *

" አንድ ዘመናዊ ዩኒቨርስቲ ሁለት ዓይነት ኃላፊነት እንዳለበት... አውስተናል:: እነዚህም የመጀመሪያው ለሚያገለግለው ሀገረ–ሰብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ለዓለም አቀፍ የዩኒቨርስቲዎች ወንድማማችነት ናቸው:: የመጀመሪያው ደካማ ከሆነ የዩኒቨርስቲው ዲግሪዎች ሊከበር የሚገባው የትምህርት ደረጃ አይኖራቸውም:: የዩኒቨርስቲው ምሩቆችም በዓለም ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጡትን ዕድል ገብተው ሊሳተፉ አይችሉም:: የመጀመሪያውን ኃላፊነት ዩኒቨርስቲው ለማካተት ወይም ለማከናወን የሚችለው ለሀገሪቱ ፍላጎት አስፈላጊ የሆነውን ጉዳይ በማስተማርና ምርምር በማድረግ ነው:: ሁለተኛውን ለማስከበር ይህንኑ ትምህርትና ምርምር ዓለም በተቀበላቸው በትክክለኛነትና በታማኝነት ደረጃዎች መፈጸም ነው:: እነዚህን መሠረታዊ ጽንሰ–ሀሳቦች ዐይነተኛ ናቸው ብለን ስለምናምን እዚህ ላይ ለአጽንዖት ደገመናቸዋል:: የዩኒቨርስቲው ግቦች በበለጠ ተቀላጥፈው ይፈጸሙ ዘንድ ላቀረብነው ሐሳብ እነዚህ ጽንሰ–ሐሳቦች መመሪያዎች ሁነው ያገለግላሉ::" ገጽ 2.

* * *

ታዲያ

<u>ምን ተደረገ</u>??

/ይህን ለአንባቢያን እንተዋለን/

## FACTS AND FIGURES

New Students Admitted to Regular Undergraduate Degree Programs by Institution and ESLCE Results for Selected Institutions (1990/91 A.Y.)

| Inst./ College | ESLCE GPA | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Below 3.2 | | 3.2 | | 3.4 | | 3.6 | | 3.8 | | 4.0 | |
| | N | % | N | % | N | % | N | % | N | % | N | % |
| Faculty of Med. (AA) | 0 | 0 | 5 | 7.69 | 1 | 1.53 | 12 | 18.46 | 43 | 66.15 | 4 | 6.15 |
| Gondar Coll. of Med. Sciences | 0 | 0 | 4 | 7.27 | 3 | 5.45 | 8 | 14.54 | 37 | 67.27 | 3 | 5.45 |
| Faculty of Vet. Med. | 0 | 0 | 0 | 0 | 19 | 47.50 | 19 | 27.50 | 2 | 5.00 | 0 | 0 |
| Jimma Inst. of Health Sc. | 1 | 1.27 | 4 | 6.89 | 0 | 0 | 8 | 13.79 | 40 | 68.96 | 5 | 8.62 |

Source: **Higher Education Main Department, Statistics on Higher Education 1990/91**, April 1992, p. 12.

**IER asks:** Apparently medical schools are getting "good" students. But do the students keep up their records? If not, why?

## FACTS AND FIGURES

New Students Admitted to Regular Undergraduate Degree Programs by Institution and ESLCE Results for Selected Institutions (1990/91 A.Y.)

| Inst./ College | ESLCE GPA | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Below 3.2 | | 3.2 | | 3.4 | | 3.6 | | 3.8 | | 4.0 | |
| | N | % | N | % | N | % | N | % | N | % | N | % |
| Faculty of Med. (AA) | 0 | 0 | 5 | 7.69 | 1 | 1.53 | 12 | 18.46 | 43 | 66.15 | 4 | 6.15 |
| Gondar Coll. of Med. Sciences | 0 | 0 | 4 | 7.27 | 3 | 5.45 | 8 | 14.54 | 37 | 67.27 | 3 | 5.45 |
| Faculty of Vet. Med. | 0 | 0 | 0 | 0 | 19 | 47.50 | 19 | 27.50 | 2 | 5.00 | 0 | 0 |
| Jimma Inst. of Health Sc. | 1 | 1.27 | 4 | 6.89 | 0 | 0 | 8 | 13.79 | 40 | 68.96 | 5 | 8.62 |

Source: **Higher Education Main Department, Statistics on Higher Education 1990/91**, April 1992, p. 12.

**IER asks:** Apparently medical schools are getting "good" students. But do the students keep up their records? If not, why?

# ትምህርት ነክ ጥያቄዎችና መልሶች ወይም አስተያየቶች

በሀገራችን ትምህርትን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ችግሮች አሉ:: ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ለመፈለግ የባለሙያዎች ክትትል አስፈላጊ ነው:: ይህን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም በትምህርት መስክ የተከሰቱትን ችግሮች ከመስክ በመሰብሰብና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥም ሆነ ውጭ ካሉ ምሁራን አስተያየት በመጠየቅ ጥያቄዎችን ከነመልሶቻቸው በዚህ ዓምድ ያወጣል::

በግልጽ ካልተጠቀሰ በቀር ለሚቀርቡት ጥያቄዎች የሚሰጡት መልሶች የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም ሳይሆኑ የመልስ ሰጪው ክፍል መሆናቸውን አስቀድመን እናስገነዝባለን::

በዚህ ዕትም ያወጣነው ዝግጅት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የመንግሥትና የመንግሥት ካልሆኑ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ኃላፊዎችና መምህራን የተገኙትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ነው:: ለጥያቄዎቹም መልስ ወይም አስተያየት በመስጠት የተባበሩን በትምህርት ሚኒስቴር /ዋናው መሥሪያ ቤት/ የሚገኙ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች፣ እንዲሁም የዳግማዊ ምኒልክና የአዲስ ከተማ ት/ቤቶች ኃላፊዎች ሲሆኑ ላደረጉልን ትብብር ከፍተኛ ምስጋና ለማቅረብ እንወዳለን::

## ጥያቄዎችና መልሶች

1. ጥያቄ፦ የባልትና ሳይንስ፣ የእርሻና የእንጨት ሥራ መምህራን ተከታታይ ሥልጠና በማግኘት በትምህርት ደረጃቸው እንዲያድጉ የሚያደርግ ሥልጠና አለ ወይ?

   - ካለ የሚሰጠው በምን አኳኋን ነው?
   - መምህራኑስ እንዴት ይመረጣሉ?
   - ሥልጠናውንስ ምን ያህል ለማዳረስ ተችሏል?

## በት/ሚር ከሁለተኛ ደረጃና የቴክኒክና ሙያ መምህራን ትምህርት መምሪያ የተገኘ መልስ

ከላይ የተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ያላቸው የሥልጠና ኘሮግ ራም እስከ 12+2 ዲኘሎማ ደረጃ ድረስ ነው ። ከዚያ በላይ መምህራኑ የትምህርት ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ በኩል አልታደ ሉም ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጣም ጥቂት የሆኑ መምህራን የውጭ ዕድል አግኘተው የትምህርት ደረጃቸውን ከፍ አድርገዋል፡፡ በተጠቀሱት ትምህርቶች የዲግሪ ኘሮግራሞች እንዲከፈቱ በተደጋ ጋሚ ተጠይቆ እስካሁን የተገኘ ምላሽ የለም ። ለባለትና ሳይንስ በአሁኑ ጊዜ አዋሳ የተከፈተ ስለሆነ በመምህራን ማሠልጠን ረገ ድም ኘሮግራም እንዲቀየስ ጥያቄው ለከፍተኛ ትምህርት ዋና መምሪያ ከሠልጣኞች ብዛት ጭምር ቀርቧል። ለእንጨት ሥራ መምህራን የናዝሬት የቴክኒክ መምህራን ትምህርት ክሊፍ ገንባታ ሥራ ሲጠናቀቅ የዲግሪ ኘሮግራም ይጀመራል፤ ለእርሻ መምህራን፤ አለማያ ገብርና ዩኒቨርስቲ ውስጥም የመምህራን ትምህርት ኘሮ ግራም እንዲቀየስ ውይይት ተጀምሮ ውጤት አላገኘም።

ለጊዜው ለተጠቀሱትና ለሌሎችም የቴክኒክና ሙያ ትምህርቶች የሁለት ክረምት የሙያ ማሻሻያ ልዩ ኘሮግራም ከ1975 ጀምሮ እየተካሄደ ነው። ምንም እንኳ ኘሮግራሙ የከፍተኛ ትምህርት ባይሆንም የደመወዝ ደረጃ ለማሳደግ ሲባል የ12+3 ተመጣጣ ኝነት ተሰጥቶታል። በአንድ ክረምት ማስተማር የሚቻለው 80 መምህራንን ነው። መምህራኑ የሚመረጡት በክልላቸው ካሉ ተመሳሳይ መምህራን ጋር ተወዳድረው ነው።.

2\. ጥያቄ፣ አንዳንድ መምህራን ኋላህ የሆነ የፈተና ጥያቄ አወጣጥ ድክመት አለባቸው። ይህ ከሆነ ስለፈተና ጥያቄዎች አወጣጥና በአጠቃ ላይም ስለማስተማር መማር ዘዴዎች ለመምህራን አጫጭር ሥልጠና ለምን አይሰጥም ? ኩየሠረ ሀሃሠኄ

## በት/ሚር ከሁለተኛ ደረጃና የቴክኒክና ሙያ መምህራን ትምህርት ፀሀመቃ የተገኘ መልስ

በአጠቃላይ በትምህርቱ ሥራ ካለው ውስብስብ ሁኔታና 
ዜው እያደገና እየሰፋ ከሚሄደው የመምህርነት ተግባር 
ጭር ሥልጠናውና አወያየሩ በየጊዜው መሻሻል እንዳለበ

በሁሉም የትምህርት መስኮች የአጫጭር ሥልጠና ፕሮግራሞች መሰጠት እንዳለባቸው አያጠያይቅም።

በመሠረቱ በአሁኑ ጊዜ ያለው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ለመምህርነት ብቁ ያደርጋል ተብሎ የሚጠበቅም አይደለም፤ ችግሩም የፈተና ጥያቄ አወጣጥ ጉድለት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለመማር ማስተማር ተግባር በሁለንተናዊ ገጽታው የተሟላ እንዳልሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል። ስለዚህ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስፈልገው በመሆኑ ስለሥልጠናው ስልት ጥናት በመደረግ ላይ ነው። በቅርብ ጊዜ ይፋ ወጥቶ ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

መሠረታዊ ለውጥ እስኪገኝ ድረስ አሁንም ባለው የሥልጠና ሥርዓት ውስጥ ስለፈተና አወጣጥ ኮርስ እንዲዘጋጅ ከዚህ ቀደም ተወስኖ በአሁኑ ጊዜ በመሰጠት ላይ ነው። አሁን በመሰጠት ላይ ያለውን ኮርስ ሳልወሰዱ ወደፊት የአጫጭር ጊዜ ፕሮግራሞች ከሚሰጡት ትምህርቶች አንዱ ይሆናል የሚል እምነት አለ።

<u>ከትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም የተሰጠ ተግባራዊ ምላሽ</u>

የጥያቄውን ክብደት በማጤንና የተቋሙንም ኃላፊነት በማገናዘብ ተቋሙ በቴስቲንግ ላይ ያተኮረ የሁለት ቀን ዐውደ ጥናት /ግንቦት 29 ና 30/84 ዓ.ም./ አካሄዷል። በዐውደ ጥናቱ ለጊዜው ለማሳተፍ የተቻለው ከሦስት የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለተውጣጡ 25 ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና መምህራን ነበር። የዐውደጥናቱንም ተሳታፊዎች በመምረጥና በማስተባበር ረገድ የአዲስ አበባ አስተዳደር አካባቢ የትምህርት መምሪያ ጉልህ ትብብር አድርጓል። የጥያቄም አቅራቢ ወደፊት በሚዘጋጀው ተመሳሳይ ዐውደጥናት ሊሳተፉ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

/ግንቦት 29 ና 30/84 ዓ.ም. በቴስቲንግ ላይ ስለተካሄደው ዐውደጥናት የቀረበውን አጭር ዘገባ በዚሁ ዕትም ከገጽ 28 እስከ 33 መመልከት ይቻላል።/

3. ጥያቄ፣ ካሁን ቀደም በየትምህርት ዓይነቱ መምህራን ሲያስተምሩ ይደረግ የነበረው ክትትልና ግምገማ በጣም እየተዳከመ መምጣቱ ይነገራል። ይህ አባባል ምን ያህል ዕውነት ነው? ከሆነስ እንዴት ሊፈጠር ቻለ? መፍትሔውስ ምንድነው?

<u>ከዳግማዊ ምኒልክ አጠ/2ኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ጽ/ቤት የቀረበ አስተያየት</u>

ግምገማውና ቁጥጥሩ የሚካሄደው በትምህርት ኢንስፔክተሮች፣ በርዕሰ መምህራን፣ በዩኒት አስተባባሪዎችና በቀዳሚ መምህራን ነበር። ግምገማውና ቁጥጥሩ የትምህርትን ጥራት ለማሳደግ፣ መምህራንን ለሥራ ለማትጋትና የሥራ ሞራላቸውን ለመጠበቅ የነበረው አስተዋጽኦ የጎላ ባይሆንም የትምህርትን ሥራ ለማንቀሳቀስ በመጠኑም ቢሆን ይረዳ እንደነበር የታወቀ ነው። በአሁኑ ጊዜ ግን ግምገማና ቁጥጥር ይካሄዳል ብሉ መናገር በጣም ያዳግታል።

ድክመቱ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ተፈጥሯል የሚል አስተሳሰብ አለን።

- በመምህራን እስታተስ / status / ዝቅ ማለት፣
- የአብዛኛው ተማሪ የትምህርት ፍላጎት መዳከም፣
- በየክፍሉ ያሉ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት
- ኢንስፔክተሮች ቀደም ሲል እንደሚያደርጉት በየወሩ እየተገኙ በግለም ሆነ በቡድን የክፍል ጉብኝት ለማድረግ አለመቻል
- ርዕሰ መምህራን በራሳቸው መተማመን አለመቻላቸውና ተቀባይነትና ተሰሚነት እንዲያጡ ገፊት መኖሩ፣
- ነባሩን የትምህርት መመሪያ መለወጥ ወይም ማስተካከል አለመቻሉ
- መምህራን በሚከተሉት የተለያዩ የፖለቲካ ዕምነት ሳቢያ በትምህርት ሙያ ላይ ያላቸው አንድነት መጥፋቱና፣ "ገምጋሚው ማን ተገምጋሚው ማን" የሚል ጥያቄ ማስከተሉ፣

- በት/ቤት ውስጥ የተደራጁት አዲስ ኃይሎች /የመምህራንና ሠራተኞች ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ፣ የትርፍ ሰዓት ሥራ ኮሚቴ፣ የመምህራን መሠረታዊ ማኅበር/ እና የት/ቤቱ አስተዳደር ተግባብተው መሥራት አለመቻል

- በተፈጠረው አዲስ የዲሞክራሲ አየር መብትና ግዴታ ተለይቶ አለመታወቅ፣

መፍትሔዎች የሚከተሉት ይሆናሉ ብለን እንገምታለን

- ዋናው መስሪያ ቤት /ትምህርት ሚኒስቴር/ ድክመት ካለበት አደረጃጀቱንና አወቃቀሩን ለማስተካከል ቢጥር

- ሥርዓተ ትምህርቱ በጥናት ግኝቶች ላይ ተመርኩዞ ቢሻሻል /ለምሳሌ 14 የትምህርት ዓይነት ከሚሆን ቀንሶትና ውህደት እንዲኖረው ሆኖ ሰብሰብ ቢል/

- ለመምህራን የተሐድሶ ኮርሶች ቢዘጋጁ፣

- መምህራን በተለያዩ መልኩ ኢንሴንቲቭ እንዲያገኙ ቢደረግ፣

- ወላጆች ት/ቤቶችና መንግሥት ተማሪው የትምህርትን ዓላማና ጥቅም አውቆ በፍላጎት እንዲማርና ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጥ የጋራ ጥረት ቢያደርጉ፣

- እውቀት፣ የሥራ ልምድና ችሎታ ያላቸውን ሰዎች በአግባቡ ብንጠቀም፣

- የሥልጣን ተዋረድ ወይም የዕዝ ሰንሰለት በውል እንዲታወቅ ቢደረግ፣ ሁኔታዎች ሊሻሻሉ ይችላሉ የሚል ግምት አለን ።

4. ጥያቄ፣ በወላጆችና በትምህርት ቤት መሐከል ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? ግንኙነቱ ለትምህርቱ ሂደት ምን ያህል ድጋፍ ሰጥቷል? ችግሮች ካሉስ ምንድናቸው?

## በአንድ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ጽ/ቤት የተገኘ አስተያየት

ትምህርት ቤታችን በመርካቶ መሐል የሚገኝ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ነው :: የበርካታ ተማሪዎች ወላጆችም መተዳደሪያ ንግድ ነው:: ከተማሪዎቻችንም መሀከል የተወሰኑት እየነገዱ እራሣቸውን በመርዳት የሚማሩ ናቸው::

በዚህ አካባቢ በአብዛኛው ወላጆች ት/ቤት በመምጣት የልጆቻቸውን የትምህርት ሂደት አይከታተሉም:: ስለልጆቻቸው ትምህርት ጉዳይ ከት/ቤቱ መምህራን፣ ዩኒት መሪዎችና ር/መምህራን ጋር ለመወያየት የሚመጡ ወላጆች ከመቶ አምስት አይበልጡም:: ብዙዎቹ ወደ ት/ቤት የሚመጡት የት/ቤቱ አስተዳደር በልጆች የፀባይ ችግር ወይም በትምህርቱ ክትትል ላይ ባለባቸው ድክመት ወላጆች እንዲያውቁ ሲፈለግና ሆን ተብሎ ሲጠሩ ብቻ ነው :: ለዚህም ፈቃደኛ ሆነው ከሚመጡት ውስጥ አባቶች ከመቶ ስላሣ አካባቢ ሲሆኑ ብዙውን ጊዜ እናቶች አለዚያም የቅርብ ዘመድ ነን ባዮች ናቸው:: ከሚመጡት ወላጁ አባቶች ውስጥ በሚነገራቸውና በተያዘላቸው ቀጠሮ ሣይሆን የእነሱን ጊዜ መወጣታቸውን አሣውቀው ቶሎ ተመልሰው ወደ ሥራቸው ሊሄዱ የሚፈልጉ በርካታ ናቸው::

ከወላጆች ጋር ውይይት ሲደረግ ባብዛኛው ለንገነዘብ የቻልነው ወላጆች ልጆቻቸውን በደንብ እንደማያውቋቸውና ት/ቤት የምን መለከተው ባህሪይ ለነሱ እንግዳ ነገር እንደሆነ ነው :: "ልጆቻችን ይህን አያደርጉም፣ ፀባየ መልካም ናቸው" የሚሉ በርካታ ናቸው :: "ሌሎች አበላሽተውት ይሆናል፣ አለበለዚያም መስሏችሁ ይሆናል እንጂ ልጄ ጥና ነው" የሚሉም አሉ :: ስለልጆቻቸው ባህሪይ አንዳንድ አስገራሚ ድርጊት ሲነገራቸው የሚደነግጡና የሚገረሙም አሉ :: ት/ቤቱ የሚወስደውን እርምጃ ስናሣውቃቸው ከዚያ ቀን በኋላ የቅርብ ክትትል ለማድረግና ከት/ቤቱም ጋር የቅርብ ግንኙነት ለመመሥረት ቃል በመግባት ይማጸናሉ :: ገን በተግባር አይተረጉሙትም ::

ተማሪዎች ወላጅ ለመጥራት ፈቃደኛ አይሆኑም፣ ወላጅ ካለመጣ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ አንፈቅድም። ይህ ሌላ ችግር ነው። ጉዳዩ ሲከፋ ከአባት ይልቅ እናት ትመጣለች። አማራጭም ካለ ሌላ ሶስተኛ ሰው ይዘው ይመጣሉ።

ወላጅ ለማምጣት ፈቃደኛ ሣይሆኑ በራሣቸው ፈቃድ ክፍል ገብተው የሚገኙ ተማሪዎችም ያጋጥሙናል። እንደ ችግሩ መጠን በስልክ ከወላጆች ጋር በመገናኘት እንዲመጡ እንጋብዛለን። ብዙውን ጊዜ የሥራ ውጥረት መኖሩንና እንደማይመቻቸው ከቤት ይገልጹልናል። ሊመጡ የሚችሉት እናቶች የቤት እመቤቶች ከሆኑ ከሥራ ሰዓት ውጪ ቀጠሮ ይያዘልናል።

ከዚህ ሁኔታ መገንዘብ እንደሚቻለው ብዙውን ጊዜ በቀላሉ ሊቀጩና ሊስተካከሉ የሚገባቸው የትምህርት ቤት ችግሮች የቅርብ ግንኙነት ማድረግ ባለመዘውተሩ የከፋ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። በቅርብ በስልክ የሚገኙትን እና ለመጥራት እንሞክር እንጂ ት/ቤቱ በወላጆች አድራሻ ሊደርስባቸው ያልቻሉትን ተማሪዎች ግን በዚሁ የዲስፕሊን ችግር ከት/ቤት ይባረራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ ቢሆንም "በቅርቡ ፈተና ለተማሪዎች አልተሰጠም ወይ? "፤" የቤት ሥራዎች እርማት አይደረግላቸውም ወይ? "፤" ከተማሪዎች ደብተር ውስጥ ምንም ልናገኝ አልቻልንም" የሚሉ ጥያቄዎች፤ "ልጆቻችን ክፍል ውስጥ የትምህርት አቀባበላቸውና የባህሪያቸው ሁኔታ ምን ይመስላል? "፤" ት/ቤት ይመጣሉ ወይስ እዚህ ከደረሱ በኋላ ተመልሰው ይወጣሉ?" በማለት አዘውትረው ከት/ቤቱ ጋር በግልጽ አንዳንዴም ከልጆቻቸው ተደብቀው የሚከታተሉና የልጆቻቸውን ባህሪይ ለማወቅ የሚጥሩ ወላጆች አሉ።

ወላጆች ከት/ቤት ጋር ግንኙነት እስካላቸው ድረስና ሌላ ችግር እስካላጋጠመን ድረስ የትምህርቱ ሂደት በታቀደው መሠረት ወደፊት ሊመራ ይችላል። የተማሪዎች የትምህርት ዲሲፕሊን ይከበራል። የሰዓት ማክበር፣ የክፍልና የቤት ሥራዎችን ማከናወን፣ ለመምህራን አክብሮት መስጠት፣ ለት/ቤት ሕግና ሥነ–ሥርዓት ተገዢ መሆን ወዘተ... ይህን መልካም ስነ ምግባር በአሁኑ ወቅት

የምናየው ከጥቂት ተማሪዎች ብቻ ነው። እነኚህም እንዱም ወላጆቻቸው ከት/ቤቱ ጋር ካላቸው ያላሰለሰ ግንኙነት ተገካሬ፣ እለበለዚያም ከቤት ቁጥጥር የማይለያቸው ተማሪዎች ይሆናሉ ብለን እንገምታለን።

ወላጆች ሙሉ በሙሉ ልጆቻቸውን ለት/ቤት አስረከበው ዞር ካሉ ከምናያቸው ብዙ ችግሮች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፦

- ለቤትና ለክፍል ሥራ ቸልተኛነት
- የጽሕፈት መሣሪያዎች እሟልቶ አለመምጣት /መማሪያ መጽሐፍንም ይጨምራል/
- የትምህርት ሰዓትን አለማክበር፣ ሲያስፈልገም አጥር ዘሎ መውጣት፣ የትም ውሎ ቤት መግባት
- ከትምህርት ውጪ ለልዩ ልዩ የሥነ-ባህሪይ ጉድለቶች ማለትም ለጫር የነት፣ ለሌብነት፣ ተደባዳቢነት፣ ለሴሰኛነት ወዘተ... መጋለጥ
- ትምህርት ቤትን የጊዜ ማሣለፊያ አድርጎ መቁጠር፣ ናቸው

* * *

## FACTS AND FIGURES

Female Enrollment in Selected Local Graduate Programs (1990/91)

| | Year I | | Year II | | Year III & above | | Total | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Inst./College | N | % | N | % | N | % | N | % |
| Faculty of Med. (AA) | 15 | 12.19 | 12 | 20.68 | 4 | 7.01 | 31 | 13.02 |
| Inst. of Lang. Studies | 6 | 20.68 | 0 | 0 | 2 | 11.76 | 8 | 13.33 |
| Demography | 0 | 0 | 1 | 25.00 | 0 | 0 | 1 | 8.33 |
| School of Information St. for Africa (SISA) | 4 | 30.76 | 0 | 0 | 4 | 30.76 | 4 | 30.76 |
| Faculty of Business and Economics | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| Faculty of Educ. | 0 | 0 | 1 | 5.55 | 1 | 5.00 | 2 | 3.63 |
| Faculty of Sci. | 1 | 2.32 | 2 | 4.76 | 1 | 6.25 | 4 | 3.96 |
| Faculty of Tech. | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| Alemaya Univ. of Agri. (AUA) | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |

Source: **Higher Education Main Department, <u>Statistics on Higher Education 1990/91</u>,** April 1992, pp. 31 & 32.

**IER Comments:** The entries for the Institute of Language Studies, SISA, Faculty of Science, and Faculty of Technology suggest that females are interested more in languages than in other fields. But look at the entries for medicine, and you will find out that their interest is not limited to languages. Would you also like to ponder over AUA's record regarding female enrollment?

# አጭር የዐውደጥናት ዘገባ

የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ የተወሰኑ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ካሰራጨው መጠይቅ ያገኘውን ጥቆማ መነሻ በማድረግ Workshop on Testing with Particular Reference to Testing in Addis Ababa High Schools በሚል ርዕስ ላይ ግንቦት 29 እና 30/84 ዓ.ም. ዐውደጥናት አካሄዷል።


በዚህ ዐውደጥናት ከሶስት የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተውጣጡ 25 ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና መምህራን የተካፈሉ ሲሆን ከእነዚህም መሀከል አምስቱ ከአዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ፣ አስሩ ከዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ፣ የተቀሩት አስሩ ደግሞ ከየካቲት 12 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመጡ ነበሩ። የዐውደጥናቱ መሪዎቹም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዶ/ር አየለ መሸሻ፣ አቶ ዳንኤል ደስታና አቶ ደሳለኝ ጫልቺሳ ነበሩ። ዐውደጥናቱም የተከፈተው በዶ/ር በኩረ ፀ/ሰማያት የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ መርሐግብር (ፕሮግራም) ኦፊሰር ሲሆን በዚሁ የመክፈቻ ስነስርዓት ወቅት ዶ/ር ዳርጌ ወሌ፣ የትምህርት ጥናትና ምርምር ተቋም ዲሬክተር፣ አቶ ኃይሌ ሽመር፣ የአዲስ አበባ አስተዳደር አካባቢ የትምህርት መምሪያ ኃላፊ፣ አቶ ቦንሣ ባይሣ፣ የአስተዳደር አካባቢው የትምህርት መምሪያ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ እንዲሁም አቶ ተፈራ ቢተው፣ የአስተዳደር አካባቢው የትምህርት መምሪያ የኢንስፔክሽን አስተባባሪ ተገኝተዋል።



የዐውደጥናቱ መክፈቻ ሥነሥርዐት በከፊል


ዐውደ ጥናቱ በአምስት ንዑስ አርዕስት የተከፈለ ነበር ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው ።

- Meaning, Purposes and Nature of Student Evaluation: An Overview
- Stating Objectives and Planning a Classroom Test
- Constructing Objective Type Questions
- Administering Tests, Scoring Test papers
- Describing Student Test performance



የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በከፊል

ከፍ ብለው በተጠቀሱት ንዑስ አርዕስት ላይ የተዘጋጀ ፀሁፍ ለተሳታፊዎቹ ታድሏል፤ በእያንዳንዱም ንዑስ ርዕስ ላይ ባለሙያዎች ማብራሪያ ሰጥተዋል፤ ከልምዱ የተገኙ ምሳሌያቸንም ለአብነት አቅርበዋል ።



የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎች በክፍል

ትምህርቱ ቲዎሪ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም በተግባር ያጋጠሙ ችግሮችን አካትቶ እንዲቀርብ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ እስከተቻለ ድረስ ልምምዱ እንዲጨመርበት ጥረት ተደርጓል። በመጨረሻም የትምህርቱ አቅራቢዎችና ተሳታፊዎች ውይይት ካካሄዱ በኋላ የዐውደጥናቱ ተሳታፊዎችም ዐውደጥናቱን በተመለከተ የተዘጋጀ መጠይቅ ሞልተዋል።

ዐውደጥናቱ ሲጠናቀቅ በቦታው ተገኝተው የመዝጊያ ንግግር ያደረጉት አቶ ኃይሌ ሽመር ሲሆኑ በዚህ ስነስርዓት ወቅት በዶ/ር ኣርጊ ወሉ እና በአቶ ኃይሌ ሽመር አማካይነት የምስክር ወረቀቶች ተሰጥተዋል።



የዐውደጥናቱ መዝጊያ ሥነሥርዓት በከፊል

ተሳታፊዎቹ በሞሏቸው መጠይቆች ላይ ከሰጧቸው አስተያየቶች የሚከተሉት ይገኛሉ ::

ሀ/ <u>ስለማስተማሪያ ፅሑፍ ብቃትና ጽሑፉ ከሥራቸው ጋር ስላለው ዝምድና</u>

ቀደም ሲል በተጠቀሱት ንዑስ አርዕስት ላይ የተዘጋጀውን ጽሁፍ በተመለከተ ከተሳታፊዎቹ መሀከል 81 % "ብቁ" ነው ሲሉ የተቀሩት 19 % ደግሞ "መጠነኛ" ነው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል :: ከዚሁ ጋር በማያያዝ ጽሑፉ ከዕለት ተዕለት ሥራቸው ጋር ያለውን ዝምድና 69 % "በጣም የተዛመደ"፣ 25 % "ደግሞ በመጠኑ የተዛመደ" መሆኑን ገልፀዋል ::

ለ/ <u>ስለትምህርቱ አቀራረብ ሂደት፣ ሁኔታና የመለመጃዎች ብቃት</u>

የትምህርቱን አቀራረብ ሂደት አስመልክቶ ከተሳታፊዎቹ መሀከል 51 % "መካከለኛ" በሆነ ፍጥነት መከናወኑን፣ 47 % ደግሞ "ጥድፊያ" የነበረበት መሆኑን ገልጸዋል ::

የአቀራረቡንም ሁኔታ በተመለከተ 62% "ከቀላል ወደ ከባድ" ማምራቱን፣ 23% "ከባድ ነገር ያየለበት" መሆኑን፣ የቀረት 15% ደግሞ "ከባድ ከቀላል ጋር በሚገባ ያልተካካበት" እንደነበር ጠቁመዋል።

ስለመልመጃዎቹም /Exercises / የብቃት ደረጃ ከተሳታፊዎቹ መሀከል 43% "በቂ"፣ 27% "መጠነኛ"፣ 16% "አነስተኛ" ናቸው ሲሉ የተቀሩት /4%/ ደግሞ ምንም አስተያየት ሳይሰጡ ቀርተዋል።

ሐ/ <u>ለዐውደጥናቱ ስለተሰጠው ጊዜ</u>

አብዛኞቹ /64%/ ተሳታፊዎቹ ለዐውደጥናቱ የተሰጠው ጊዜ "አነስተኛ" መሆኑን ጠቁመዋል። የቀረት /32%/ "መጠነኛ" ነው ሲሉ፣ 4% ደግሞ "በቂ" በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

መ/ ተሳታፊዎቹ ያላቸውን ማንኛውንም አስተያየት እንዲሰጡ ለቀረበላቸው open-ended ጥያቄ ከጻፏቸው መልሶች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- "በዐውደጥናቱ ላይ የተጠቀሱ፣ የቀረቡ ነገሮች እጅግ በጣም ጠቃሚ ናቸው ብዬ ባምንም የተሰጠው ጊዜ አናሳ በመሆኑ እንደልብ ተወያይቶ ለመማማር አለመቻሉና ጊዜው ሰፋ ቢል የተሻለ ይመስለኛል"
- "የዚህ ዓይነቱ Workshop ለሁሉም ት/ቤቶች የሚዳረስበት መንገድ ቢፈለግ ጥሩ ነው"
- "የዐውደጥናቱ ጊዜ ከማጠሩና በዚህም የተነሳ ገለጻ ባልሆኑት አንዳንድ ርዕሶችና ንዑስ ርዕሶች ለመወያየት ካለመቻሉ በስተቀር ለትምህርቱ ሥራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋልና ቀጥሉበት እላለሁ"።

<u>ማጠቃለያ</u>

ከተሳታፊዎቹ አስተያየት አንፃር ሲታይ ዐውደጥናቱ ጠቃሚ ነበር ለማለት ይቻላል። ሆኖም፣

- የዚህ የዐውደጥናት ጊዜ / duration / ቢራዘም
- አቀራረቡም ደረጃ በደረጃ /ከቀላል ወደ ከባድ/ እንዲሆን የበለጠ ጥረት ቢደረግ እንዲሁም
- መልመጃዎቹ የበለጠ ቢዳብሩ

የዐውደጥናቱ ጥቅም ከፍተኛ እንደሚሆን ይገመታል።



የጠደፈቱ አቅጣጫ ሲጤን

## <u>FACTS AND FIGURES</u>

Percentage of Full-Time Ethiopian Female Teaching

Staff in AAU (1990/91 A.Y)

| College | Diploma | | Bachelors | | Masters | | Doctorate | | Total | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | N | %* | N | %* | N | %* | N | %* | N | %* |
| Faculty of Med. (A.A) | 2 | 100.00 | 0 | 0 | 2 | 50.00 | 4 | 7.27 | 8 | 12.90 |
| Gondar Coll. of Med. Sc. | 3 | 37.50 | 1 | 20 | 0 | 0 | 1 | 5.88 | 5 | 14.70 |
| Awassa Coll. of Agri. | 0 | 0 | 3 | 23.07 | 1 | 6.66 | 0 | 0 | 4 | 10.52 |
| Faculty of Sc. | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 | 10.00 | 1 | 3.03 | 4 | 5.71 |
| Faculty of Educ. | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 9.52 | 1 | 10.00 | 3 | 6.97 |
| School of Pharmacy | 0 | 0 | 3 | 33.33 | 0 | 0 | 0 | 0 | 3 | 21.42 |
| Inst. of Lang. Stud. | 0 | 0 | 1 | 12.50 | 2 | 7.69 | 0 | 0 | 3 | 6.81 |
| Faculty of Vet. Med. | 1 | 25.00 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 4.00 | 2 | 5.55 |
| Bahir Dar. Teach. College | 1 | 10.00 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| College of Social Sciences | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 6.66 | 0 | 1 | 2.32 |
| Faculty of Bus. & Econ. | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| Faculty of Law | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| Factulty of Tech. | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |

* Out of the total (males & females) for the category.

**<u>Grand Total:</u>** Male = 539
Female = 33

Source: **Higher Education Main Department, <u>Statistics on Higher Education 1990/91</u>**, April 1992, pp. 53-58

**<u>IER notes</u>:** Compare the figures for the School of Pharmacy and Gonder College of Medical Sciences with those of the College of Social Sciences and the Facutly of Law. Do you see what we mean?